# ኢትዮጵያ፡ ከግንቦቱ ምርጫ በፊት አፈና እየጨመረ ነው

## መንግስት የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችን፣ የመገናኛ ብዙሃን እና ተሟጋቾችን እያስፈራራ ነው

(ናይሮቢ፣ መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም) - የኢትዮጵያ መንግስት ከግንቦት 2002 ምርጫ በፊት በፖለቲካ ተቀናቃኞቹ፤ በጋዜጠኞችና በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ላይ ተከታታይና የተቀነባበረ ጥቃት መክፈቱን የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆነው ሂውማን ራይትስ ዎች በዛሬው እለት ባወጣው መግለጫ አስታወቀ፡፡ ኢትዮጵያውያን ውዝግብና የደም መፋሰስን ካስከተለው የ1997ቱ ምርጫ በኋላ የመጀመሪያውን የፓርላማ ምርጫ ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ያደርጋሉ፡፡

ሂውማን ራይትስ ዎች «ተጽዕኖ የማድረግያ አንድ መቶ መንገዶች፤ የመደራጀትና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት ጥሰት በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ያወጣው ባለ 59 ገጽ ሪፖርት የኢትዮጲያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የተቃዋሚ ደጋፊዎችን በብዙ ዘዴዎች እየቀጣቸው መሆኑን ይገልጻል፡፡ ፓርቲው ከ1997 ምርጫ በኋላ ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠራቸው የቀበሌና የወረዳ መዋቅር በኩል ተቃዋሚዎች የግብርና ግብአቶች፤ አነስተኛ ብድሮች፣ የሥራ ዕድሎች እና መሰል አገልግሎቶችን እንዳያገኙ በማድረግ ይጨቁናቸዋል፡፡ በቅርብ ጊዜ የወጡ ህጎችም ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ለመገናኛ ብዙሃን እንቅስቃሴ ማናቆ መሆናቸውን ሪፖርቱ ይገልጻል፡፡

«ኢትዮጵያ ውስጥ ተቃውሞን መግለጽ በጣም አደገኛ ነው» የሚሉት የሂውማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዳይሬክተር ጆርጂያት ጋኖ «መንግሥትና ገዢው ፓርቲ አንድ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ መንግስት ተቃዋሚዎችን ለማጥፋትና ህዝቡን በማስፈራራት ጸጥ ለማሰኘት ሙሉ ስልጣኑን ይጠቀማል» ብለዋል፡፡

መንግስት በሚፈጽመው አፈና ምክንያት በርካታ የሲቪክ ማህበረሰብ ተሟጋቾችና ጋዜጠኞች በቅርቡ ሀገር ጥለው ተሰደዋል፡፡ በታህሳስ ወር 2002 ዓ.ም ተቀባይነት ያለው ነጻ ጋዜጣ የተዘጋ ሲሆን ባለፈው ወር ደግሞ መንግስት የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የሚሰራጭበትን ሞገድ አፍኗል፡፡ ኢትዮጵያውያን ከፍርሃት ነጻ ሆነው መናገር፤ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደዚሁም በምርጫ ፤ በጽሁፍና በሰላማዊ ሰልፍ የመንግስታቸውን ፖሊሲ መቃወም አይችሉም፡፡ መንግስት በ2001 ዓ.ም. የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ፕሬዝዳንት የሆኑትን ብርቱካን ሚደቅሳን ከህግ ውጭ አስሯል፡፡

ኢትዮጵያ በውጭ እርዳታ በእጅጉ የምትደገፍ ሲሆን አንድ ሶስተኛ ያህል የመንግስት ወጭዋ የሚሸፈነውም በእዚሁ ነው፡፡ የአገሪቱ ዋነኛዎቹ ለጋሾች የሚባሉት የአለም ባንክ፤ አሜሪካ፤ እንግሊዝ እና የአውሮፓ ህብረት እየተበላሸ የሄደውን የመንግስት የሰብአዊ መብት አያያዝን በመተቸት ረገድ የተለሳለሰ አቋም መያዛቸውን ሂውማን ራይትስ ዎች ገልጿል፡፡

ሂውማን ራይትስ ዎች ሪፖርቱን ለማጠናቀር 15 ቀናት የፈጀ ጥናት በኢትዮጵያ ያካሄደ ሲሆን በወቅቱ 200 የሚሆኑ ሰዎች ጋር ቃለመጠይቅ አድርጓል፡፡ ገበሬዎች፣ መምህራን፤ የመንግስት ሠራተኞች፤ የመብት ተሟጋቾች፤ የተቃዋሚ ፓርቲና የመንግስት ባለስልጣናት እንደዚሁም በዋና

ከተማይቱ አዲስ አበባና በሌሎች ሶስት የክልል ከተሞች የሚገኙ የእርዳታ ድርጅት ሃላፊዎች እና ዲፕሎማቶች ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መካከል ይገኙበታል።

ኢህአዴግ በሚያዚያ 2002 ዓ.ም. 99.9 በመቶ ካሸነፈበት የአካባቢ እና ማሟያ ምርጫ ወዲህ በቀበሌና በወረዳ አስተዳደሮች ያለውን ቁጥጥር ያጠበቀ ሲሆን ህዝቡን በፍጹም የበላይነት እያስተዳደረ ይገኛል። ሂውማን ራይትስ ዎች በጎበኛቸው አካባቢዎች እያንዳንዱ መንደር በትንንሽ ቡድኖች እንዲደራጅ መደረጉን እና የአካባቢው ባለስልጣናትና ታጣቂዎች እያንዳንዱ ቤተሰብ የተቃውሞ ምልክቶች እንዳያሳይ እንደሚቆጣጠሩት ከነዋሪዎች ተረድቷል። የአካባቢ ባለስልጣናት ገዢውን ፓርቲ የማይደግፉ ወይም መንግስትን የሚተቹ ሰዎችን መንግስታዊ አገልግሎት እንዳያገኙ በማድረግ ይቀጧቸዋል።

የአካባቢ ባለስልጣናት በነዋሪዎች አኗኗር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አላቸው። ባለስልጣናቱ በምግብ-ለሥራ መርሀግብር የሚሳተፉ ሰዎችን በመምረጥና በመቆጣጠር፤ መደበርያና ምርጥዘር በማከፋፈል፤ የአነስተኛ ብድር አገልግሎትን በማደረስ፤ ለሥራ፣ ለትምህርትና ሥልጠና የድጋፍ ደብዳቤ የመጻፍ ሃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። ህዝቡ ቤተሰቡን ለማስተዳደር እና ሥራውን ላለማጣት የገዥውን ፓርቲ ከመቀላቀል ውጭ ሌላ አማራጭ ስለሌለው አባሎቻችን እየቀነሱብን ነው ሲሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች  ቅሬታ ያሰማሉ። መንግስት በስሩ ያሉ ሰራተኞችን በተለይም መምህራን አባሎቹ እንዲሆኑ ያስገድዳቸዋል፤ ተሰሚነት ያላቸውንም እየለየ ይቀጣቸዋል። የመንግስትን አፈና ለማጋለጥ የሞከረ የሲቪክ ማህበረሰብ ተሟጋቾችን ለማሸማቀቅ አስፈሪዎቹን የበጎ አድራጎትና ማህበራትን አዋጅና እንደዚሁም የጸረ-ሽብር ህግን ይጠቀማል።

ሂውማን ራይትስ ዎች የኢትዮጵያ መንግስት ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞችን በመልቀቅ የምርጫ ምህዳሩን እንዲያሻሽል ጥሪ ያቀርባል። መንግስት ለሁሉም ባለስልጣናት እና የኢሕአዴግ አባላት በፖለቲካ ተቃዋሚዎች፤ በሲቪክ ማህበራትና የብዙሃን መገናኛዎች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃትና ወከባ እንዲያቆሙ  ይፋዊ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ ጥሪ ያቀርባል። መንግስት አለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎችን ጨምሮ በተናጠል እየቀረቡለት ያሉትን በመብት ጥሰት ላይ ምርመራ የማድረግና ይፋዊ ሪፖረት የማቅረብ ጥያቄዎችን እንዲፈቅድም ጠይቋል።

አለም ዓቀፍ ታዛቢዎችን በመላክ የግንቦቱን ምርጫ ለመታዘብ እያሰቡበት ያሉ አካላት ቢኖሩ የአውሮፓ ህብረት እና የአፍሪካ ህብረት ብቻ ናቸው። በበጎ አድራጎትና ማህበራት ላይ የተጣለው ገደብ ሀገር በቀል የግል ታዛቢዎች የማሰማራትን ጉዳይ የማይታሰብ አድርጎታል። ሂውማን ራይትስ ዎች ሁሉም አለም አቀፍ ታዛቢዎች በቅድመ ምርጫ ወቅት የነበረውን ወከባ ምርጫው ነጻ እና ፍትሃዊ ስለመሆኑ ግምገማ በሚያደርጉበት ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ጥሪ ያቀርባል።

«የኢትዮጵያ የውጭ አጋሮችም ዝምታቸውን ሰብረው በአገሪቱ የነገሰውን ፍራቻ መኮነን አለባቸው» የሚሉት ጋኛን «ለጋሾች ዳጎስ ያለ የገንዘብ ዕርዳታቸውን የተቃዋሚዎች ማዋከብ እንዲያበቃ፣

የሙብት ተሟጋቾችንና የብዙሃን መገናኛዎችን ለማፈን የወጡትን ህጎች ለማስቆሚያነት መጠቀም አለባቸው» ብለዋል፡፡

## <u>ከሪፖርቱ የተመረጡ</u>

«ማወቅ ያለብህ ነገር ቢኖር እያንዳንዱ ነገር በኢሕአዴግ ርዕዮተ-ዓለም መሰረት በሰፈር ደረጃ የተዋቀረ መሆኑን ነው፡፡ ሁሉም ነገር የተደራጀውና ቁጥጥርም የሚደረገው በትናንሾች የሰፈር ቡድኖች ነው፡፡ ተቃዋሚ ከሆንክ ከመንደሩ ኑሮ ትገለሳለህ፡፡»
***መምህር- ከአማራ ክልል***

«እኔ የኢሕአዴግ አባል ነኝ፡፡ ነገር ግን ተቃዋሚ ፓርቲን እደግፋለሁ፡፡ አባል መሆን ማለት ምንም ማለት አይደለም፡፡ የእርዳታ እህል ስለምፈልግ የኢሕአዴግ አባል ነኝ . . .ለፓርቲው የመዋጮ ክፍያ ያደረግሁበትን ማረጋገጫ ይዞ መገኘት የእርዳታ እህል ለማግኛት እንደ መስፈርት ይፈለጋል፡፡ መዋጮውን የምከፍለው መጨቆንም ሆነ መገለል ስለማልፈልግ ነው፡፡»
***የገዢው ፓርቲ አባል- ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል***

«ከፍተኛ የሆነ ግለ-ሳንሱር አለ፡፡ ብዙ የምናውቃቸው ግን የማንጽፋቸው ታሪኮች አሉ፡፡ብዙ ነገርም አውጥተን አንናገርም፡፡ ቀዩ መስመር የት እንደተሰመረ አልተነገረንም፤ መገመት ግን አለብን፡፡ የእነርሱ የሽብር አተረጓጎም (በጸረ-ሽብር ሕጉ ውስጥ) ሰፊ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለእኛ በጣም አደገኛ ነው፡፡ ለምሳሌ አንዱን የፖለቲካ ፓርቲ አሸባሪ ነው ብለው ከሰጡበት እኛ ስለዚያ ድርጅት መጻፍ አንችልም... ጋዜጦች ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ ውጤት ከመግለጹ በፊት ስለምርጫ ውጤት የህዝብ አስተያየት መስኪያ ማድረግ ወይም ግምታቸውን መተንበይ አይፈቀድላቸውም፡፡»
**ጋዜጠኛ-** ***አዲስ አበባ***

«የተጽዕኖ ማድረጊያ አንድ መቶ መንገዶች፡ የመደራጀትና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት ጥሰት በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ የወጣውን ሙሉ ሪፖርት ለማንበብ [http://www.hrw.org/node/89128](http://www.hrw.org/node/89128) የሚለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ፡፡

-ሂውማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያ ላይ ያወጣቸውን ሪፖርቶች ለማየት ከፈለጉ [www.hrw.org/en/africa/ethiopia](http://www.hrw.org/en/africa/ethiopia) የሚለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ፡፡